# ይህ ማን ነው?

እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ። ወደ ጌታ ቤት መምጣት በጣም ደስ ይላል።

2 ከቅርብ ጊዜ በፊት፡ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እያደረግሁ ይመስለኛል፡ በማነብበትም ቦታ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲቃረብ፡ ደቀ መዛሙርቱ ዓይናቸውን አንሥተው ቅድስት ከተማዋን ከሩቅ አይተው፡ “አሁን መንግሥቱ ተመልሶ ይመጣል፡” እያሉ፡ በደስታ መናገር ጀመሩ ይላል።

3 ይህ ሰውዬ እየተናገረ የነበረው፡ በቅርቡ ወደ ፍልስጤም ስላደረጉት ጉብኝት፡ እየተናገረ ነበር፡ ባለፈው ዓመት ሰዎች፡ እዚያ ቦታ ሲመጡ ነበር ብሏል፡ እነርሱም ከሸለቆው ወጥተው ሲመጡና ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ፡ በዚያን ጊዜ የሄዱበትን መንገድ ዙሪያውን ሲመለከቱ፡ ከተማዋን ሲያዩ፡ ማልቀስ ጀመሩ።

4 ታውቃላችሁ፡ በወቅቱ የነበሩት ደቀ መዛሙርት፡ መንግሥቱ፡ ዳግመኛ እንደሚቋቋም፡ ተ—ተሰምቷቸው ነበር፡ ብዬ አምናለሁ።

5 አሁንም ጊዜው ደርሷል። በሕዝቡ ላይ ያለው ስሜት ይህ ነው ብዬ አምናለሁ፡ መንግሥቱ እንደገና ለመመለስ ዝግጁ ነው ማለት ይቻላል።

6 ወንድም ኔቪል፡ መልካምና የተባረከ ፓስተራችን፡ ከጥቂት ሌሊቶች በኋላ፡ እዚህ ተብርናክል ስለሚያካሄደው ሪቫይቫል፡ እንድጸልይ ነግሮኛል። የተባረከ ነገር ይሆናል ብዬ አስቤ ነበር፡ አልኩት።

7 በጣም ብዙ ሪቫይቫል ሊኖራችሁ አይችልም። ብዙ ጊዜ ስለ ተሃድሶ የተሳሳተ ሃሳብ እናገኛለን። ሪቫይቫል ማለት አዳዲስ አባላትን ማምጣት ሳይሆን፡ ነገር ግን አሁን ያለንን ለ... ለማነቃቃት ነው።

8 ይህን ማለት እወዳለሁ፡ ምክንያቱም ይህን የምለው ከልቤ ነው። በተብርናክል ዙሪያ ለረጅም ጊዜ ከነበረው የተለየ ስሜት እየተሰማኝ ነው፡ ከረጅም ጊዜ በ—በፊት፡ እንደነበረው፡ ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ስሜት እየተሰማኝ ነው፣ የሚረጋጋና፡ እውነተኛ መሠረት ያለው ነገር ነው። እግዚአብሔር ይህችን ትንሽ ቤተክርስቲያን እንደገና በስልጣኑ እንደሚባርክ አምናለሁ፡ እና... ? ... ።

9 የግንባታ ፕሮግራሙ እየተካሄደ መሆኑን አይቻለሁ፡ ያ በጣም ጥሩ ነገር ነው ብዬ አሰባለሁ። ምክንያቱም፡ በቅርብ ጊዜ ወይም ቆይተንም ቢሆን፡ እኛ በዕድሜ የገፋን ሰዎች የጦር ትጥቃችንን አውልቀን ለልጆቻችን መልሰን እንሰጣቸዋለንና፡ በዚያ ወርቃማው መሰላል ላይ እንወጣለን።

10 በቀደም የሃምሳ ዓመት፡ የእድሜዬን ግማሽ ማለፍ ችያለሁ። ያንን ብቻ መገንዘብ አልችልም። አሥራ ሰምንት አሥራ ሰድሰት አሥራ ሰምንት ዓመት ገደማ አከባቢ እያለሁ፡ ለክርስ መሰነር፡ በግሮሰሪዎች ውስጥ ሰስራ ከነበርኩበት ጊዜ፡ ብዙ የሄደ አይመስልም። ነገር ግን ጊዜው በፍጥነት ሄዷል። ይህ የሚያሳየው እዚህ ዘላቂ የሆነ ከተማ እንደሌለን፡ ወደፊት የሚመጣውን

ከተማ እንደምንጠብቅ ነው። ይህች ከተማ ግንባታዋ ከእግዚአብሔር ነው፡ ፍጻሜዋም ከቶ የለም።

11 ዛሬ ጠዋት፡ በእናቶች ቀን ጉዳይ ላይ እየተናገርኩ ነበርና፡ እናትን አርጅታ እንዳለች ላለመቀበል እየሞከርኩ ነበር፡ በእርጅና፡ ፊቷ ተሸብሽቦ፡ እና ይህ ሁሉ፡ በክራንች እየሄደች፡ ወይም አሮጌ ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ተቀምጣ፡ ወይም በአርምቼር ወንበር ተቀምጣ፡ በአጠገቧም ትንሽ የአበባ ማሰሮ ተቀምጦ ማሰብ አልፈልግም፣ ነገር ግን እናት በትንሣኤዋ፡ ወደ ወጣትነቷ ተመልሳ፡ እንደ ንግሥት እያንጸባረቀች፡ ትቆማለች። ስለ እናቴ ማሰብ የምወደው በዚህ መንገድ ነው። ዛሬ ባለችበት ሁኔታ አርጅታ፡ ማሰብ አልፈልግም። የሚመጣውን ማሰብ ደስ ይለኛል። ስለ እናቶቻችሁ እንደዚህ እንደሚሰማችሁ አውቃለሁ። በልቧ ውስጥ እንዳለች አስቧት። ገ... ገጣሚው እንደሚለው፡ "ሕይወት ለእርሷ ቀላል አልነበረም፡ ነገር ግን ለእናንተ አንድ ነገር ለማድረግ ስትል፡ ሁሉንም እንደገና ትኖራለች።" ስለዚህ እግዚአብሔር እሷ ከእናንተ ጋር ለዘላለም መኖር የሚትችልበትን መንገድ ያዘጋጃል። በእሷም ደስተኛ ነኝ።

12 ለምን እንደሆነ አላውቅም፡ ዛሬ ጠዋት፡ ይህንን ማስታወቂያ አወጣሁ፡ ዛሬ ማታ፡ እግዚአብሔር፡ ቢፈቅድ፡ **ይህ ማን ነው**? በሚል ርዕስ እናገራለሁ ብዬ አሳወቅኳችሁ በእርግጥ እንዴት እንደሚናገር አላውቅም። ነገር ግን ከሰዓት በኋላ ቃለ መጠይቅ እያደርኩ፡ እስከ አንድ ሰዓት ከአሥር ደቂቃ በፊት ድረስ በስራ ተጠምጄ ነበር፡ ልዩ ልዩ የ—የአስቸኳይ ጊዜ ጥሪዎች ነበሩኝ። እነሱን ማድረግ አልቻልኩም።

13 ለዶክተር ሳም መጸለያችሁን እንድትቀጥሉ እፈልጋለሁ። ደኅና እ— እየሆነ ነው፡ ለዚህም እናመሰግናለን። ዶክተር ባልድዊን እና ወይዘሮ ባልድዊን ሁለቱም እያገገሙ ነው። ደህና እየሆኑ ነው።

14 ዛሬ ከሰዓት በኋላ በጸሎት ዝርዝራችሁ ላይ፡ አዲስ ሰው እንድትጨምሩ እፈልጋለሁ። ይህም ሃሪ ሊስ ነው፡ የመድሃኒት ባለሞያ። ሃሪ የግል ጓደኛዬ ነው። እሱን ሳውቀው፡ ክርስቲያን ነው ብዬ አስበው ነበር፡ እስከ ዛሬ ከሰዓት በኋላ፡ ወንድሙ ለነፍሱ መዳን ጥያቄውን እስኪያቀርብ ድረስ። ወንድም ማይክ ኢጋን... የኛ ባለአደራ፡ ወሬውን ነገረን። ሃሪም በከባድ ሁኔታ፡ ሆስፒታል ውስጥ ይገኛል። ስለ እኔ ያን ያህል እንደሚያስብ አላውቅም ነበር፣ ነገር ግን ዛሬ ከሰዓት በኋላ የራሱን ፓስተር፡ ወይም የሚሄድበትን ቤተክርስቲያን ፓስተር እምቢ ብሎ፡ እሱን ለማየት እንድመጣ ጠየቀኝ። እሱን ለማየት መሄድ እፈልጋለሁ። ስለዚህ፡ ለሃሪ ጸልዩ።

15 ከጆርጂያ፡ የመጡ ወዳጆቼን፡ ወንድም፡ ዌልች ኢቫንስንና፡ ቤተሰቡን፡ እዚህ በማየታችን ደስ ብሎናል። በተጨማሪም፡ የማላውቃቸው ሌሎች የመጡትን፡ ዛሬ ጠዋት እዚህ ተገኝተው፡ አያቸዋለሁ።

16 ካልተሳሳትኩ፡ ከኋላ ወንድም እና እኅት ኤልመር ኮሊንስ፡ ከፊኒክስ፡ አሪዞና አያቸዋለሁ። ኦህ፡ አልተቀየራችሁም። ያኔ ከትራኩ ስትወጡ፡ የባቡር ሐዲድ ላይ ስትሰሩ የ—የምትለብሱትን ልብስ እንደለበሳችሁ ይመስላል። ወደ ቤታችሁ እንኳን በደህና መጣችሁ! እዚህ እንድትቆዩ ልጠይቃችሁ አልችልም፡ ምክንያቱም የተሻለ ቦታ ስላገኛችሁ፡ አያችሁ፡ ያ በጣም ጥሩ ነው፡ ፊኒክስ። አንድ ቀን እኔ ራሴ፡ እዚያ መኖር፡ እፈልጋለሁ።

17 ከቼርች ኦቭ ጋድ የመጣውን፡ ወንድም ሰሚዝን፡ በዚያ አየዋለሁ። ወንድም ሰሚዝ፡ በቀደም ምሽት፡ ወይም ትናንት ከሰዓት፡ በኋላ፡ ትንሹ መጽሐፍህ፡ ተሰጥቶኛል። ገና አላነበብኩትም፡ ነገር ግን እንተ እስከጻፍክ ድረስ፡ በእርግጠኛነት አነበዋለሁ። እውነተኛ፡ ትክክለኛ ቅዱሳት መጻሕፍት መሆን አለበት። እግዚአብሔር ይባርክህ። ስኬታማ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ።

18 ሌሎች ብዙዎቻችሁ፡ እንኳን ደህና መጣችሁ ማለት እችላለሁ። ሁላችሁም እዚህ ተብርናክል እንኳን ደህና መጣችሁ። ዛሬ ጠዋት ሲሰተር ሰትሪከር የዘመረችውን መዝሙር፡ በጣም ወድጄዋለሁ፡ “በቀዳዳው በኩል፡ ወደ እሷ እየተመለከተ ነው” የሚለውን። የሜኖኒት እምነት ተከታዮች የሆኑ ወንድሞቼ፡ እዚህ በመገኘታቸው ደስ ብሎኛል። እና፡ ኦህ፡ ስለሁላችሁም ደስ ብሎኛል! ከኢሊኖይ የመጣ፡ አንድ ጓደኛዬ፡ ይመስለኛል፡ ልጁ ከጀርባው ቅጂዎችን እየወሰደ ነው፡ ዳግመኛ ልናገኛቸው እንችላለን። ብዙዎቻችሁ፡ ስ… ስማችሁን ካልጠራሁ ያላየኋችሁ እንዳይመስላችሁ፡ ነገር ግን ሁላችሁንም በደስታ እንኳን ደህና መጣችሁ እላችኋለሁ።

19 በዛሬው ምሽት፡ ከቅዱሳን መጻሕፍት የምናገኘው ትምህርት እናንብበው፡ በማቴዎስ ምዕራፍ 21 ላይ የሚገኘውን፡ ከ1ኛው ቁጥር አንሥቶ፡ እስከ 11ኛው ቁጥር፡ ድረስ ያለውን ሃሳብ፡ ያጠቃልላል።

> **ወደ ኢየሩሳሌምም ቀርበው፡** ወደ ደብረ ዘይት **ወደ ቤተ ፋጌ፡ ሲደርሱ፡ ያንጊዜ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት ላከ፡ እንዲህም አላቸው፡**
>
> **አላቸውም፡ በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፡ በዚያን ጊዜም የታሰረችን አህያ ውርንጫም፡ ከእርሰዋ ጋር ታገኛላችሁ፥ ፈትታችሁ፡ አምጡልኝ።**
>
> **ማንም አንዳች ቢላችሁ፡ ለጌታ ያስፈልጉታል፡ በሉ፣ ወዲያውም ይሰዳቸዋል።**
>
> **ለጽዮን ልጅ፡ እነሆ ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያ ላይና፡ በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ፡**
>
> **እንዲህ በሏት… ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል፡** በሉአት፡ **ተብሎ በ**… በነቢይ የተነገረው፣ **ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆነ።**
>
> **ደቀ መዛሙርቱም ሄደው፡ ኢየሱስ እንዳዘዛቸው አደረጉ፡**
>
> **አህያይቱንና፡ ውርንጫዋንም አመጡለት፡ ልብሳቸውንም በእነርሱ ላይ ጫኑ፡ ተቀመጠባቸውም።**
>
> **ከሕዝቡም እጅግ ብዙዎች ልብሳቸውን በመንገድ ላይ አነጠፉ፣ ሌሎችም ከዛፍ ጫፍ ጫፋን እየቈረጡ፡** በመንገድ ላይ ያነጥፉ ነበር።
>
> **የሚቀድሙትም፡** ሕዝብ **የሚከተሉትም፡ ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ፡ በጌታ ስም የሚመጣ፡ የተባረከ ነው፡ ሆሣዕና፣ በአርያም እያሉ ይጮኹ ነበር።**

**ወደ ኢየሩሳሌምም በገባ ጊዜ፡ መላው ከተማ፡ ይህ ማን ነው? ብሎ ተናወጠ፡**

**ሕዝቡም፡ ይህ የናዝሬቱ ነቢዩ ኢየሱስ ነው አሉ...**

ለጸሎት አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

20 ኦህ ጌታ ሆይ፡ በዚያ ዘመን ኖረን ቢሆን ኖሮ ምን እንል ነበር፡ ብለን ራሳችንን እንጠይቃለን። እኛ ግን እርሱ የሚመጣበትን ታላቅ ቀን፡ እየተጠባበቅን ነው። ጌታ ሆይ፡ በዝግጅት ላይ እያለን፡ ልባችንን እያዘጋጀን፡ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ካሉት፡ ከመከር እርሻዎች የምንሰበስባቸውን እህል ሁሉ እያመጣን፡ ነጭ ፈረስ ላይ ተቀምጦ፡ እርሱ ሲመጣ የምናየውን ጊዜ እያሰብን እና እየተጠባበቅን ነው፡ ከክብር በሮች ሲወርድ፡ ይህን አሮጌ ሟች አካላችንን በመለወጥና በመቅረጽ፡ ከራሱ ጋር ወደሚመሳሰል ወደ ከበረው አካል ይለውጠዋል፡ በዚያም ኃጢአትም ሆነ የሞት ምልክት ሊገባ አይችልም። ደግሞም እርሱን እንዳለ እናየዋለን፡ በሕይወትም እንኖራለን፡ በሚመጡት ዘመናት ሁሉ እንወደዋለን።

21 ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ለፓስተሯ፡ እና ለአስተዳዳሪዎቿና ለዲያቆኖቿ፡ እንዲሁም ወደዚህ ስለሚመጡ ሰዎች ሁሉ እናመሰግናለን፣ እንዲሁም ወደቤታችን ደጅ የሚመጡ ጎብኚዎች ሁሉ ባርካቸው፡ እነዚህም በተመሳሳይ ጉረኖ ውስጥ ያሉ፡ ነገር ግን ከሌላ ጉረኖ የመጡ በጐች ናቸው። 1ዛሬ ማታ፡ በመገኘትህ፡ እንዲባርኳቸው እንጠይቃለን።

22 ዛሬ ማታ፡ ከዚህ ቦታ የምንወጣው፡ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ፡ የተሻልን ክርስቲያኖች ለመሆን ቁርጠኛ በመሆን እንዲሆን ቃልህን መግበን። በልባችን አዲስ ተስፋ ይኑረን፡ በደስታም፡ የእርሱን መምጣት እንጠብቅ።

23 በአጋጣሚ በመካከላችን፡ የታመሙና የተሠቃዩ ቢኖሩ፡ ለእነሱ መጸለይ እንረሳም። ያም እነዚያ... ዛሬ ማታ፡ ለዓምልኮ ወደተሰበሰብንበት፡ ሕንጻ በመግባት፡ ሲመጡ፡ የታመሙ ካሉ፡ ደኅና ሆነው ይውጡ።

24 እንዲሁም በቤት ውስጥም ሆነ በሆስፒታል፡ እንዲሁም በአልጋ ላይ፡ የሚያገግሙትን እንድትፈውሳቸው እንጠይቃለን። አምላካችን ሆይ፡ ምሕረትህ እንዲደርስላቸው፡ እንጸልያለን።

25 ዛሬ ማታ፡ ለእነዚያ ችላ ላሉት፡ ጌታ መልካም መሆኑን ገና ላልቀመሱት እና ላላዩት፡ በእግዚአብሔር መወደድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለማያውቁ እንጸልይላቸዋለን። የሚጎድላቸውን አይረዱም። አምላኬ ሆይ፡ የሆነ የሬዲዮ ስርጭቶች፡ ወይም በሆነ መንገድ፡ ልባቸውን ይነካ፡ ምህረት ወደ ሌለው ፍርድ ለመቅረብ የምህረት በር ከመዘጋቱ በፊት፡ ስሜታቸው ወደ አንተ ይዙር።

26 ጌታ ሆይ፡ እርዳን። እነዚህን ነገሮች በጌታ በኢየሱስ ስም እንለምናለን፡ ለክብሩም እንጠይቃለን። አሜን።

27 ሰዎች በበሩ ዙሪያ እጅግ ተጨናንቀው የነበረ ሲሆን፡ ጎዳናዎችም በሰዎች ሞልተው፡ የሚተኙበት ቦታ እንኳን አልነበራቸውም። ይህ የፋሲካ በዓል ስለነበር፡ ከቅጥሩ ውጭ፡ በየአቅጣጫው ተኝተው ነበር። በዚያን ወቅት ለማምለክ፡ ከመላው ዓለም የሚመጡ ሰዎች ነበሩ። የፋሲካ በግ የሚታረድበት ጊዜ ነበርና። ይ... ይህ በዓል እስራኤላውያን ከግብፅ ባርነት፡

ነጻ መውጣታቸውን የሚያመለክት ነበር። ይህንንም በየአመቱ፡ ይጠብቁታል። በየዓመቱ፡ ይህን ታላቅ የፋሲካ በዓል ያከብሩ ነበር። ይህም በአይሁድ ሃይማኖት ውስጥ እጅግ አስደናቂ ከሆኑት ጊዜያ ወ… ወይም ክስተቶች ውስጥ አንዱ ነበር፡ ምክንያቱም ነጻ የወጡበት ጊዜ ስለሆነ።

28 ሁሉም ሰው ነጻ የወጡበትንም ጊዜ፡ ማሰብ ይወዳል። ዛሬ ማታ፡ እያንዳንዳችን፡ ነጻ የወጣንበትን ጊዜ ወደ ኋላ መለስ ብለን ማሰብ የምንችለው እንዴት ነው! ይህ ለእኛ ምን ማለት ነው!

29 እኔ ራሴ በራሴ ተሞክሮ፡ ምስኪኑ ልቤ እግዚአብሔርን ለመንካት እንዴት እንደጓጓ ማስታወስ እችላለሁ። እንዲህ እያልኩ እሰቤ ነበር፡ “ኦህ፡ ወደ ላይ ወጥቼ በሩን ባንኳኳ፡ ለጥቂት ጊዜ ቢያወራኝ!” በእርግጥም፡ ታሪኬን፡ ታውቁታላችሁ። ወረቀትና እርሳሴን አንስቼ፡ ደብዳቤ ሊጽፍለት ነበር፡ ምክንያቱም ከእሱ ጋር መነጋገር አልቻልኩም ነበር። እርሱ በጫካው ውስጥ እንደሚኖር አውቅ ነበር፡ ምክንያቱም እርሱን ሰምቼው ነበር፡ በጫካው ውስጥ ሲንቀሳቀስ አይቼው ነበር። ለ—ለማደን ወይም አሳ ለማጥመድ ስሄድ በሚሄድበት ጊዜ፡ ከዚህ በፊት በሚሄድበት በተለመደው መንገድ እየሄድኩ ነበር። እኔም፡ “ደብዳቤውን በዛፉ ላይ እያጣበቅኩ፡ ይድረስ ለሚስተር ኢየሱስ” ብዬ አሰብ ነበር። ይህ ሸክም ከልቤ ሊወርድ የሚችልበት ብቸኛው መንገድ ነው።

30 እነሆ፡ በወዲያ ማዶ፡ በዚያች ምሽት! እድሜዬን እረሳለሁ፡ አልፎ ተርፎም ስሜን ልረሳው እችላለሁ፡ ነገር ግን ከኃጢአት ያዳነኝን ያን ጊዜ መቼም ቢሆን አልረሳውም። ይህም በጨለማ ውስጥ ታላላቅ ቀናቶችን እንዳልፍ ረድቶኛልና፡ በውስጤ የሆነ ነገር ሆነ። ነጻ የወጣሁ ጊዜ፡ የኃጢያት ሸክም ትቶኝ ሄደ፡ እኔም አዲስ ሰው ሆንኩ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት ሆንኩ።

31 እነዚህ አይሁዶች፡ በየዓመቱ፡ ወደዚህ ይመጣሉ። በቤተክርስቲያን ውስጥ ም—ምንጭ ነበር። እ—እነሱም እንጀራውን አምጥተው፡ መራራውን ቅመማ ቅመም አዘጋጅተው፡ የበግ ጠቦቱንም አርደው ይበላሉ፡ ከቤተክርስቲያኑ ምንጭም ይጠጣሉ። እንዲሁም እግዚአብሔር ሞገሱን ስላሳያቸው አንድ ላይ ተሰብስበው አብረው ተደሰቱ። ስለዚህ፡ ያ የፋሲካ ወቅት ስለነበረ፡ ፋሲካ ብቻ ሳይሆን፡ ልዩ የፋሲካ በዓልም ነበር።

32 ታውቃላችሁ፡ አንዳንድ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንሄዳለን… ሁልጊዜ መሄድ እንወዳለን፡ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ልዩ የሆነ ነገር ይፈጠራል።

33 ይህ ከእነዚያ ጊዜያት አንዱ ነበር። አየሩ ልክ እንደዛሬው፡ በተስፋ ተሞልቶ ነበር። እርሱን የሚወዱ ሁሉ እርሱን በበሩ ውስጥ እንዲገባ እየተጠባበቁ ነበር።

34 በዛሬው ጊዜም ቢሆን ሁኔታው በእጅጉ ተመሳሳይ ነው ብዬ አምናለሁ፡ ምክንያቱም እሱን የሚወዱ ሁሉ እሱን እየፈለጉ ነው። አየሩ በተስፋ የተሞላ ነው።

35 አሁን በዚህ ዘመን ስንኖር፡ በእርግጥ የምንኖረው፡ ምድር ታላቅ የዱቄት በርሜል በሆነችበት ዘመን ነው። ሳይንስም እንደሚነግረን፡ “እኩለ ሌሊት ሊሞላ ሁሉም ነገር ሊበላሽ ሦስት ደቂቃ ብቻ ነው የቀረው” ይላል። እርግጠኛ ነኝ በቀደም፡ እኔ እንዳነበብኩት፡ በሠራዊቱ ውስጥ ስለ ጄኔራሉ ታሪክ፡

እያነበባችሁ እንደነበረ፡ ይህም፡ “ሌላ ጦርነት ቢነሣ፡ ሁለት ወይም ሦስት ደቂቃዎችን ብቻ ይቆያል፡” አለ። የድሮው የጦር ትግል፡ የጠመንጃ ተኩስ፡ የምሽግ ጉድጓድ መቆፈር፡ ያ ሁሉ አልፏል። የሚቀጥለው ጦርነት ሁለት ወይም ሦስት ደቂቃ ብቻ እንደሚሆን ይናገራሉ። አንድ ቀን፡ እነሆ አንድ አዕምሮው-የጎደለው ሰው ከቁጥጥር ውጪ ይሆንና ከቦምቦቹ ውስጥ አንዱን ይተኩሳል። ይህን ሲያደርጉ፡ የተተኮሰውንን ለመከላከል እኛም ለመከላከል ወደዛ መተኮስ እንዳለብን፡ በሁላም ቦታ፡ አዋጁን እንሰማለን። ዓለም ያንን መቋቋም አትችልም።

36 በፋሲካ በዓል ላይ የተገኙት ሁሉ አንድ ነገር ይሆናል ብለው ይጠባበቁ ነበር፡ ነገር ግን ምን እንደሆነ እያውቁትም ነበር።

37 ዛሬም ሁኔታው እንደዚያው ነው። ሁሉም ሰው የሆነ ነገር ሊሆን መሆኑን ያውቃል። ሁሉም ሰው ያንን ያውቃል። ኃጢአተኛውን ብታነጋግሩት፡ ነጋዴውም ብታነጋግሩት፡ ከማንኛውም ሰው ጋር መነጋገር ትችላላችሁ፡ እና፡ ኦህ፡ ይህ ለዓለም በጣም አስጨናቂ ጊዜ ነው።

38 ነገር ግን የእርሱን መምጣቱን የሚጠባብቁትን ወንድ ወይም ሴት ብታነጋግሯቸው ግን፡ የሚበራው፡ ክብሩ በፊታቸው ላይ ነው። ያንን ታላቅ ክስተት እየተጠባበቁ ነው። ስለዚህ ሁሉም አየር እንደገና ተሞልቷል፡ የሆነ ነገር ይሆናል ብለው በመጠባበቅ ላይ ናቸው። ዓለም ምን ሊሆን እንደሚችል አያውቅም፡ ነገር ግን የሕያው የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ምን እንደሚሆን ታውቃለች። በቅርብ መለከት እንደሚነፋ ያውቃሉ፡ ከክብር ወጥቶ፡ በነጭ ፈረስ ላይ ተቀምጦ፡ በክብር ሲመጣ እናያለን፡ የሰማይም ሠራዊት ይከተሉታል። ክርስቶስን አምነው የሞቱት በአየር ከእርሱ ጋር ለመገናኘት ከሞት ተነስተው ይወሰዳሉ። እየጠበቅን ያለነው ይህንኑ ነው። እየናፈቅነው ነው።

39 ዛሬ ጠዋት ስለ እነዚያ እናቶች ነፍሶቻቸው፡ እና ስለሌሎች፡ እንደተናገርነው፡ ከእግዚአብሔር መሠዊያ በታች ሆነው፡ እየጮኹ፡ “ጌታ ሆይ፡ እስከመቼ? እስከመቼ? ” ይላሉ እናንተ እናታችሁን ለማየት ከምትጓጉት በላይ እነርሱ ሊያዩኣችሁ ይናፍቃሉና። የምንወዳቸው ሰዎችም እኛ እነሱን ለመገናኘት እንደምንፈልግ ሁሉ እነርሱም እኛን ለመገናኘት ይፈልጋሉ።

40 እርሱ ሲመጣ፡ እንዴት ያለ መገናኘት ይሆናል! ከምንወዳቸው ሰዎች ጋር ለመገናኘትና በትንሣኤ አካላቸው ለማየት፡ የተከበረ፡ ከትንሳኤው ወራሾች ጋር ለመራመድ፡ እንዴት እንደተለወጠ፡ ባህሪያቸውን ለመመልከት፡ የዋህነታቸውና ጸጥታቸውን ለማየት እንናፍቃለን። ሁከትና ግርግር፡ መዝለልና መባነን አይሆንም፡ ለዘላለም አብረን ለመኖር ለዘለዓለም አለን።

41 ኦህ፡ ይህ አሁን የምንኖርበት ታላቅ ዘመን የሰከረ ዘመን ነው፡ ለምንም ነገር ምንም ጊዜ የለም፡ መውጣት፡ መባነን፡ መያዝ ብቻ ነው፡ ለምን፡ በጣም አስፈሪ ዘመን ነው።

42 ከዚያም፡ አንድ ነገር ይሆናል ብለው ሲጠርባበቁ የነበሩ፡ በፋሲካ ላይ ከነበሩት መካከል ብዙዎቹ እርሱን ማየት ባለመቻላቸው በጣም አሳዛኝ ነበር። ይሁን እንጂ፡ አንድ ነገር ሊሆን እንደሚችል ያውቁ ነበር፡ ሆኖም ኢየሱስን ማየት አልቻሉም ነበር።

43 በጌታ መምጣትም እንዲሁ ይሆናል። ዛሬ፡ አንድ ነገር ሊከሰት መሆኑን የሚያውቁ፡ ብዙ የተረበሹ ሰዎች አሉ፡ ነገር ግን እሱን በ—በጭራሽ አያዩትም። በእኩለ ሌሊት በጸጥታ ይመጣልና፡ እርሱን ለማየት የምትናፍቀውንና የምትጠባበቀውን ያቺን ትንሽ ቤተክርስቲያን ለመውሰድ ይመጣል። መጥቶ የሚወስዳቸው እነዚያን ናቸው። በቅንጦት የሚኖሩና፡ ነፍሳቸውን በዓለማዊ ነገሮች የሚመግቡ ብዙ ሰዎች፡ ቤተክርስቲያን ወደ ክብር እስክትገባ ድረስ፡ ምን እንደተፈጠረ አያውቁም፡ ምክንያቱም እርሱ በሌሊት እንደ ሌባ ይመጣልና ይወስዳቸዋል። ስለዚህ አሁንም ተመልሰን ወደ ተመሳሳይ ሁኔታ እንደደረስን ማየት እንችላለን። አሁን የምናገኘው፡ ይህ፡ ይህ ተሰፋ፡ እግዚአብሔር የሚመጣው... በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ሁሉ፡ ተመሳሳይ ነገር ነው። ሁ... ሁሌም ለሚጠብቁት፡ ሁሌም ሊያዩት ለሚፈልጉት ይገኛል። ዛሬም ማታ በልባችን ውስጥ ያለው ተሰፋ ይህ እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ።

44 ከስድስት ወር ገደማ በፊት ይመስለኛል፡ ለአንዳንድ ሰዎች፡ እየመሰከርኩ ነበር። እኔም እንዲህ አልኩ፡ “ኦህ፡ ለማሰብ ያህል፡ እሱ በማንኛውም ጊዜ ሊመጣ ይችላል!”

45 ይህን ለማለት ያነሳሳኝ፡ ወንድም ቦስዎርዝ ነው። ያንን ሽማግሌውን ቅዱስ ሰው ለማየት በሄድኩበት ጊዜ፡ እየሞተ መሆኑን ሰንሰማ፡ ዕድሜው ሰማንያ-ዓመት ገደማ ነበር፡ እኔና ባለቤቴ ከ... ከመሞቱ በፊት እሱን ለማየት ወደዚያ እየሄድን ነበር። አንድ ነገር ብቻ መናገር ነበረብኝ። ቅዱሳን ወደ ክብር ሲገቡ ማየት ደስ ይለኛል፡ እሱን ማየት ነበረብኝ። በጣም በፍጥነት ነድተን ነበር የሄድነው።

46 ነገር ግን እዚያ ደርሼ፡ ወደ በሩ ስጣደፍ፡ ሽማግሌውን አባት ጥግ ላይ አስተኝተውታል። መምጣቴን ሲያይ አንገቱን ቀና አደረገ። ያረጁት፡ ደካማ እጆቹ፡ ወደ ታች ከወጣ ስጋ ጋር በተሸበሸበ ቆዳ ተንጠልጥለውል። እጆቹንም ለእኔ ለሰላምታ ሰጠኝ። እኔም አንገቱን አቀፍኩና እንዲህ ብዬ ጮህኩኝ፡ “አባቴ፡ አባቴ፡ የእስራኤል ሰረገሎችና፡ ፈረሰኞች፡” እርሱ ቅዱስና እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ነበርና።

47 እኔም፡ “ወንድም ቦስዎርዝ፡ አንድ ነገር ልጠይቅህ እፈልጋለሁ። እፈወሳለሁ ብለህ ታምናለህን? ” አልኩት

እርሱም፡ “ኦህ፡ ህመም እንኳ አልታመምኩም” አለ።

እኔም፡ “እሺ፡ ምን ሆነህ ነው? ” አልኩት

48 እርሱም፡ “ወደ ቤት እሄዳለሁ” አለኝ። እርሱም፡ “ደክሞኛል፡ በጣም ደክሞኛል። ወደ ቤት መሄድ ብቻ ነው የምፈልገው” አለኝ።

49 እኔም፡ “ከዚያም እየሞትክ መሆኑን ተገንዝበሃልን? ” አልኩት፡ “አንድ ነገር ልጠይቅህ እፈልጋለሁ። በአገልግሎት ካሳለፍካቸውን ሰባ-ከሚያህሉ ዓመታት፡ መለስ ብለህ ስታሰብ ከሁሉ የላቀው ጊዜህ የትኛው ነው? ወዳጄ፡ የነበረህን ታላቅ ጊዜ መቁጠር ከቻልክ፡ ባሳለፍከው ጊዜ፡ ምን ዓይነት ተሞክሮ እንደነበረህ፡ ልትነግረኝ ትችላለህ” አልኩት።

50 የእሱን ዕድሜ ለማየት በሕይወት እኖራለሁ፡ መቼም አልረሳውም፡ በእነዚያ መነጽሮች አናት ላይ አሸግረው፡ እነዚያ ጥቁር ዓይኖች ሲያዩኝ ነበር። እንዲህ

አለኝ፡ “ውድ ወንድሜ፡ የሕይወቴ ታላቁ ጊዜ ይህ ነው። ከአሁን የበለጠ ግርማ ሞገስ የተሞላበት ጊዜ ማሰብ አልችልም።”

51 ፊቱን ተመለከትኩና፡ እንዲህ አልኩ፡ “ወዳጄ፡ አሁንም እየሞትክ መሆኑን ታውቃለህ? ”

52 እንዲህ አለ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ እዚህ ተኝቻለሁ፡ ያንን በር እንዲከፍትና እንዲመጣ ከራሱ ጋር እንዲወስደኝ፡ በየደቂቃው እየጠበቅኩት ነው።” ይሄ ነው የምሞትበት መንገድ። ይሄ ነው የሚሄድበት መንገድ።

53 እንደምታውቁት፡ ያ፡ ከመሞቱ ከሁለት ሰዓት በፊት ከ... ከሁለት ቀናት በላይ፡ ኮማ ውስጥ፡ ተኝቶ ነበር። ወደ አእምሮው ሲመለስ፡ በክፍሉ ውስጥ ተነሥቶ፡ ከሚስቱ ጋር መነጋገር ጀመረ። ከዚያም፡ በድንገት፡ ንቁ ሆነ። ከአርባና ከሃምሳ ዓመታት በፊት ከሞቱት፡ ከጓደኞቹ ጋር፡ ለአንድ ሰዓት ወይም ከዚያ በላይ ያህል፡ ተጨባበጠ። እነዚያም እርሱ ወደ ቤተክርስቲያን ያመጣቸው ሰዎች ናቸው። ከእናቱ እና ከአባቱ ጋር እጁን ተጨባበጠ። ህ... ህይወቱ ከሰውነቱ ወጣች፡ በአልጋው ላይ በትራስ ተኝቶ፡ በጌታ በኢየሱስ እቅፍ እንቀላፋ። እርሱን ማገልገልን፡ እርሱን መጠበቅን የመሰለ ነገር የለም።

54 ከዚህ ሰው ጋር ስነጋገርና፡ ያንን ተሞክሮ ሲነግረኝ፡ እንዲህ አልኩት። እኔም፡ “ወዳጄ፡ ኦህ፡ እርሱን ስናይ ክብር አይሆንምን? ኦህ፡ ዛሬ ቢመጣስ” አልኩ!

እርሱም “ወንድም ብራንሃም፡ ሰዎችን እንደዚህ አታስፈራራቸው፡” አለኝ።

እኔም “ምን ማለትህ ነው፡” አልኩት?

55 እርሱም፡ “ኦህ፡ ዓለም እየመጣ ነው፡ ወይም ክርስቶስ እየመጣ ነው ብለህ ለሰዎች ለመንገር አትሞክር። ያሳስባቸዋል” አለኝ።

56 “ኦህ፡” እንዲህ አልኩት፡ “አይ። ይቅርታ አርግልኝ። ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን ለመውሰድ ሊመጣ መሆኑን መስማት፡ እርሱን ለሚጠብቁት እጅግ አስደናቂ ዜና ነው፡ ኢየሱስ ወደ ቤተክርስቲያኑ ሊገባና ቤተክርስቲያኑን ሊወስድ መሆኑ።” እርጅና በወጣትነት ይተካል። በኀዘን ፋንታ ደስታ ይሰጣል። በሞት ፋንታ ሕይወት ይሰጣል። ሟችነት በዘላለማዊነት፡ ይተካል። ኦህ፡ እሱ እንደሚመጣ ማወቁ፡ ምንኛ አስደሳች ነው!

57 እርሱን እየፈለጉት ነበር። እርሱን እየጠበቁት ነበር። እርሱ ሲመጣ፡ ሁለት ወገኖች ነበሩ። አንደኛው ቡድን ከእርሱ ጋር የሚስማሙ ሲሆኑ፡ ሌላኛው ደግሞ የማይስማሙት ነበር።

58 ዛሬም የምናገኘው በዚህ መንገድ ነው። ይህ ነው፡ የእርሱ መምጣት፡ ሁሌም ህዝቦችን ይከፋፍላል። ሁል ጊዜ፡ ኢየሱስን ስታገኙ፡ በዙሪያው ያሉትን ከእሱ ጋር የሚቃረኑትን ታገኛላችሁ። ያ ሰይጣን ነው። እና፡ ዛሬም፡ ይህን ስናስበው፡ ብዙ ለውጥ አናይም። ልክ እንደዛው ተመሳሳይ ነው። ሰዎች ተለውጠዋል፡ ነገር ግን የሰዎች መንፈስ አልተለወጠም።

59 እነሆ በስተመጨረሻ ግን ወደ ደጅ አማትረው ሲያዩ፡ በትንሿ ነጭ አህያ ላይ ተቀምጦ፡ ሲመጣ አዩት፡ ደቀ መ—መዛሙርቶቹ “መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች!” እያሉ መጮኽ መጀመራቸው አያስደንቅም፡ ሕዝቡም ሊገናኘው ሮጠ፡ ኢየሩሳሌምም ሁሉ ተናወጠች። ስለ እሱ የሆነ ነገር አለ፡ ኢየሱስ ሲመጣ፡

ሁሌም የሚናወጥ ነገር አለ። መላው ከተማም ተናወጠ። ይ—ይህንንም መደበቅ አልቻሉም።

60 በወቅቱ የነበሩት ሰባኪዎችም ለዚህ ነውጥ ትኩረት ሰጡ፡ ምክንያቱም በፋሲካ በዓል ወቅት ስለነበረ ነው። “ይህ ማነው?” ብለው ጮኹ፡ አየሩ ሲሞላ፡ ጌታ ኢየሱስ፡ ወደ ኢየሩሳሌም መምጣቱ፡ አየሩን በተስፋ ሲሞላ፡ መምህራኑ ምን ሊከሰት እንደሚችል ማወቅ ያለባቸው ይመስላል። ሊቀ ካህናቱም ሆነ ሌሎቹ ካህናት ይህን የሚያውቁ ይመስል ነበር። ሌሎቹ ካህናት ሁሉ የሚያውቁት ይመስላል።

61 መንፈስ ቅዱስ የጌታ የኢየሱስን መምጣት አስቀድሞ ስለሚያስታውቅ፡ ዛሬም ቢሆን፡ አልተለወጠም። መንፈስ ቅዱስም በምድር ላይ መስፋፋት ሲጀምር፡ የሪቫይቫል እሳቶች በየቦታው፡ ተነስተዋል፡ ታላላቅ ምልክቶችና ድንቆች ተፈጽመዋል፡ ፈውሶች ተፈጽመዋል፡ ትንቢቶች ተነገሩ። የሐዋርያዊ ቡራኬዎች በሙሉ እንደገና ወደ ቤተክርስቲያን ተመለሱ። ስለዚህ፡ በዚያን ጊዜ እንደነበረው ሁሉ፡ አሁንም ቢሆን፡ የማያምን ሰው መንፈስ “ይህ ማን ነው?” ብሎ ይጮኻል፡

62 አንዳንዶች ጌታ ኢየሱስን ያመኑት፡ እርሱም ጥሩ ሰው ነው ለማለት ነው። አንዳንዶች፡ “እርሱ ጥሩ ሰው ነው” ይላሉ።

63 ዛሬም የሚናገሩት ይህንኑ ነው። እንደ ናፖሊዮን፡ እንደ ተዋጊ ሊያስቀምጡት ይሞክራሉ። እ—እንደ ጆርጅ ዋሽንግተን በማስመሰል፡ ሀቀኛ ሰው እንደሆነ አድርገው ማስመሰል ይሞክራሉ። ነገር ግን እርሱ ከዛ በላይ ነው።

64 የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎችን አስተውላችኋል? ስለ እርሱ፡ “ይህ ከገሊላ የመጣ ነቢይ ነው፡” ይላሉ።

65 ዛሬም ይህን ታላቅ የእግዚአብሔርን እርምጃ ሲመለከቱ፡ ተመሳሳይ ነገር ለመናገር ይሞክራሉ፡ የታመሙትንና፡ የተጐዱት፡ ወደ ጤንነት ሲመለሱ፡ መንፈስ ቅዱስን በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ሲጠቀም ሰያዩ፡ የሰዎችን ሃሳብ ሚስጥር ሲገልጥ፣ እንደሚፈጸም የተናገረውን ነገር ለመፈጸም፡ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ እንዳደረገው ሁሉ አሁንም ሲያደርግ ሲመለከቱ፣ በእርግጥም ቤተክርስቲያናትና ሕዝቡ፡ ይህን ይጠይቃሉ፡ “ይህ ማን ነው?’”

66 ኢየሱስ ማን እንደሆነ አልገባቸውም ነበር፡ ምክንያቱም በትምህርታቸው፡ ማንም ሊያውቀው አልቻለም። “ከየትኛው መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ነው የመጣው? ከየትኛው የሥነ መለኮት ትምህርት ቤት የመጣ ነው?”

67 ዛሬም እንደዚያው ነው። በመንፈስ ቅዱስ የተቀቡት አብዛኞቹ ሰዎች ከየትኛውም ሴሚናሪ አልመጡም። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር ራሱ የመረጣቸው ናቸው። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የተገቡ ምልክቶች፡ ተአምራትና ድንቆች፡ በመንፈስ ቅዱስ ተገልጠው በህዝቡ መካከል ይንቀሳቀሳሉ።

68 ዛሬ እንዲህ ይላሉ፡ “ከየትኛው ትምህርት ቤት ናቸው?” ሪቫይቫል ለማድረግ፡ ወደ አንድ ከተማ ስትገቡ ወዲያውኑ “የየትኛው የሃይማኖት ተቋም አባል ነህ?” ብለው ይጠይቃሉ፡

69 አርብ ከሰዓት በኋላ፡ በሉዊቪል ከሚገኘው የአየርላንድ ቤተክርስቲያን ከሮማ ካቶሊክ ቄስ ጋር ቃለ መጠይቅ አድርጌያለሁ። ያ ጥሩ ምሁር ሰው፡ ራሴን እንዳስተዋወቅሁት፡ እንዲህ አለኝ፡ “ሚስተር ብራንሃም፡ ከየትኛው ሃይማኖት ተቋም ጋር ነህ? ”

እኔም፡ “ከማንም ጋር አይደለሁም” አልኩት።

እርሱም ታዲያ፡ “ተሹመሃል? ” አለኝ፡

እኔም፡ “አዎን፡ ወዳጄ” አልኩት።

እርሱም “ማን ሾመህ? ” አለኝ።

70 እኔም፡ “ጌታ ኢየሱስ ወንጌልን እንድሰብክ፡ መንፈስ ቅዱስን ሰጠኝ፡ ተልዕኮም ሰጠኝ” አልኩት። ደህና፡ እኛ የሚያስፈልገን ሹመት ያ ነው።

71 ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ፡ “ወደ ዓለም ሁሉ ሄዱ... ” እነዚህን ነገሮች እየነቀፍኩ አይደለም፡ ነገር ግን ዘመናቸውን አሳልፈዋል። “ሂዱ፡ **ለ-በርካታ** ዓመታት፡ አገልጋይ ለመሆን ጥናት አድርጉ፡” አላለም።

72 “ከሰማይ የሚመጣውን ኃይል እስክትለብሱ ድረስ፡ በኢየሩሳሌም ከተማ ቈዩ፡” አለ። ይህን የተናገረው የራሳቸውን ሰም መፈረም ለማይችሉ ሰዎች ነው። “ከዚህ በኋላ፡ መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ ይመጣል፡ ከዚያም በኢየሩሳሌም፡ በይሁዳ፡ በሰማርያ፡ እንዲሁም እስከ ምድር ዳር ድረስ፡ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ” አላቸው። ያ ሹመት ነው።

73 ኢየሱስ የትኛውንም ትምህርት ቤት ስለመሄዱ፡ ወይም ከየትኛውም ሴሚናሪ ስለመመረቁ ምንም መረጃ የለንም። ሆኖም፡ በሃይማኖታዊ ምክንያቶችና፡ በዓለም ላይ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ፡ በ—በሱ ሰም ብዙ ሴሚናሮች ተቋቁመዋል። ወደ ትምህርት ቤት ስ—ስለመሄዱ ምንም መረጃ የለንም። ነገር ግን፡ አሁንም፡ ከሰማይ በታች ካሉት ሰዎች ሁሉ በላይ በሰሙ የተገነቡት ትምህርት ቤቶች፡ ብዙ ናቸው። እርሱ መጽሐፍ ሲጽፍ አናውቀውም። ይሁን እንጂ፡ ከተጻፉት ጽሁፎች ሁሉ ስለእርሱ የተጻፉት ይበዛሉ። በዛሬ ጊዜም፡ በመላው ዓለም ከሚገኙት መጻሕፍት ሁሉ፡ እጅግ ተወዳጅ የሆነው፡ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

74 ነገር ግን፡ እያችሁ፡ የጉብኝት ቀን ሲመጣ፡ “ይህ ማን ነው? ” ብለው ጮኹ፡

75 እያችሁ፡ እግዚአብሔር ምንም የማይመስለውን ነገር ወስዶ፡ አንድ ነገር እንዲፈጥር ያደርገዋል። አምላክ የሚያደርገውም ያ ነው።

76 ወደ በሩ፡ ሲመጣ ሲያዩት፡ አንዳንዶቹ፡ “ይህ ታላቅ ሰው ነው” አሉ።

77 ዛሬም እንዲሁ ይላሉ። በዛሬው ጊዜ፡ ኢየሱስ ታላቅ ሰው እንደነበር፡ ጥሩ ሰው እንደነበረ፡ የሚያስተምሩ የሃይማኖት ትምህርት ቤቶች አሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ነቢይ ነበር ይላሉ። አሁን፡ እርሱ ነቢይ ብቻ ቢሆን፡ ወይም መልካም ሰው ቢቻ ቢሆን ኖሮ፡ በኃጢአታችን ውስጥ ነበርን። እርሱ ከነቢይ በላይ ነበር። እርሱ ከመልካም ሰው በላይ ነበር። ሆኖም፡መልካም ሰው ነበር። ሆኖም፡ ነብይ-የሆነ እግዚአብሔር ነበር። እርሱ ግን ከዚያ በላይ ነበር። እርሱ ኃጢአትን ለማስወገድ፡ በሥጋ የተገለጠ አምላክ ነበር።

78 እርሱም እየጋለበ፡ ሲመጣ፡ ብዙ ሰዎች፡ "ይህ ሰው ፈዋሽ ነው። ኦህ፡ የዓይነ ሰውራን ዓይን ሲከፍት አይተነዋል። ሽባዎች እንዲሄዱ ሲያደርግ አይተናል። ሲጸልይ፡ ከዚያም ትኩሳት ልጁን ሲለቀው አይተናል" ይላል። ነገር ግን፡ ከዚያ፡ እነዚህ ሰዎች ኢየሱስን የተከተሉት ለዳቦውና ለዓሣው ብቻ ነበር።

79 በዛሬው ጊዜ ብዙ ሰዎች፡ እንዲህ ናቸው። ፈዋሽ ካለ፡ ለምን፡ እርሱን ይ—ይከተሉታል፡ እ—እርሱም ምንጭ ነው። ከታመሙ፡ ይሮጣሉ፡ እንዲህ ይላሉ፡ "ኦህ፡ እባክህ ጌታ ኢየሱስ እንዲፈውሰኝ፡ ትጸልይልኛለህ?" ከሆስፒታል፡ ወይም ከህመምተኛ አልጋ እንደወጡ፡ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚሉት፡ ልክ ውሻ ወደ ትፋቱ፡ ወይም አሳማ ወደ ጭቃ እንደሚመለስ፡ ወዲያው ወደ ዓለም ይመለሳሉ። ከእርሱ ለሚያገኙት መልካም ነገር ብቻ ይከተሉታል። እርሱን የ—የሚጠቀሙት እንደ ቶቴም ምሰሶ ለምልክትነት ብቻ ነው፡ ወይም ከ—ከእርሱ ሊያገኙ ለሚችሉት ነገር ነው፡ ነገር ግን እርሱን ለማገልገል አይፈልጉም። ያ ሕዝብ ዛሬም እንደቀጠለ ነው።

80 ከለምጽ ዘጠኝ ሰዎች ተፈውሰው ነበር፡ ይሁንና አንዱ ብቻውን እርሱን ለማመስገን ተመለሰ። ወይስ አሥሩ ነበሩ? ከእነዚህ መካከል፡ አንዱ፡ እርሱን ለማመስገን ተመለሰ፡ ሌሎቹ ደግሞ ሳያመሰግኑ፡ ቀጠሉ።

81 በአሜሪካ ውስጥ ያሉ ሰዎች፡ በእግዚአብሔር ኃይል የተፈወሱ፡ ልባቸውን ወደ እግዚአብሔር ቢመልሱ ኖሮ፡ በዚህ ሀገር ውስጥ ሪቫይቫል ይሆን ነበረ፡ ይህም እያንዳንዱን የኮንትሮባንድ ቦታ ሁሉ ይዘጋ ነበር... የመጠጥ ሱቆች እና የዊስኪ ሱቆች ከሰዕሉ ይጠፉ ነበር። አብያተ ክርስቲያናት ይሞሉ ነበር። እሁድ ምሽት ቲያትሮች ባዶ ይሆኑ ነበር። በዚህች ሀገር ውስጥ፡ ሪቫይቫል ይነሳ ነበር። ይሁን እንጂ፡ እግዚአብሔር የሚያደርጋቸውን ነገሮችን ሲመለከቱ፡ አሁንም፡ "ይህ ማን ነው? ይህ እየመጣ ያለው ማነው? ከየት ነው የመጡት? ይህ ማን ነው? በምን ሥልጣን ነው ይህን የሚያደርገው?" ብለው ይጮኻሉ

82 በጆሃንስበርግ፡ ደቡብ አፍሪካ፡ መቼም አይረሳኝም። ከሰላሣ ደቂቃ በፊት፡ አውሮፕላን ተሳፍሬ ነበር፡ የመጣሁት። በአየር ላይ ሶስት ቀንና ሌሊት ስለነበርኩ፡ ደክሞኝ መቋቋም አልቻልኩም ነበር። ወ—ወደ ኀምሳ ወይም ወደ ሥልሳ ሺህ የሚጠጉ ሰዎች ወደተሰበሰቡበት ሜዳ ወሰዱኝ። መድረክ ላይ እንደወጣው ወዲያው፡ በመንፈስ ቅዱስ እንዲህ እስኪሆን ድረስ... ባ—ባስ፡ ወደ ቦታው ሲመጣ፡ አየሁ። በላዩም፡ "ደርባን" የሚል ምልክት ነበር። አንድ ወጣት ከአባቱና ከእናቱ ሾልኮ ወጥቶ ሲለይ አየሁት፡ አንደኛው እግሩ ከሌላው ሰድስት ወይም ሰምንት ኢንች ያነሰ ነበር። ነጭ ሸሚዝ፡ ከሱሪውን ከፍ አድርገው የሚይዝ ማሰሪያ ካለው ሱሪ ጋር ለብሷል። እኔም ወጣቱን ተመለከትኩት። ወደ ኋላ ተመለከትኩ። ራእዩ ጠፋ። ከዚያም፡ ወዲያው፡ ከኋላ በኩል መብራት በጉባኤ መካከል፡ በአንድ ወጣት ላይ አብርቶ አየሁ። እኔም ተመለከትኩት። "የሆነ ቦታ አይቼዋለሁ፡" ብዬ አሰብኩት። ተመለከትኩት፡ ያም ብርሃን ለጥቂት ደቂቃዎች በላዩ ላይ እያበራ ቆየ። ተርጓሚው የሚቀጥለውን ቃል እስኪተርግም እየጠበቅኩ ነበር። ከዚያም ያ ወጣት ቆሞ፡ ክራንቹን ሲጥል አየሁ፡ ሰድስት-ኢንች-አጭር የነብረው እግሩ ከቀሪው እግር ጋር እኩል ሆነ።

83 ዛሬ ማታ በክብር ለሚገኘው፣ ለአቶ ኤጄ ሾማን፡ እንዲህ አልኩት።

“ሚስተር ሾማን፡ ቃሌን ተናገር። ራእይ ነው፡” አልኩት።

እሱም፡ “በጣም ጥሩ” አለኝ።

84 እኔም እንዲህ አልኩት፡ “በኋላው የተቀመጠው ነጭ ሸሚዝና፡ የሚንጠለጠል ሱሪ የለበሰው ወጣት ልጅ፡ ከአገሪቱ አሥራ አምስት መቶ ማይል ርቀት ላይ ከምትገኘው፡ ደርባን ከምትባል ከተማ፡ በአውቶቡስ ነው የመጣው። ወደዚህ ለመምጣት፡ ከአባቱና ከእናቱ አምልጦ ነው የመጣው። ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ አመነ፡ አንዱ እግሩ ከሌላው ሰድስት ኢንች ያነሰ ነው።”

85 ወጣቱ ልጅ ዘሎ ተነሥቶ ቆመ። እነሆ፡ ቆሞ፡ ክራንቹን መፈለግ ጀመረ። እኔም፡ “አንተ ወጣት ልጅ፡ ጌታ ኢየሱስ ፈውሶሃል” አልኩት። ወዲያውኑ እግሩ፡ ወደ ትክክለኛው እግር ሰድሰት ማይል አደገ፡ ከቀረው ጋር እኩል ሆነ። ወጣቱን ወደ መድረኩ አምጥተው፡ ዶክተሮች መረመሩት። መጽሐፌ ላይ ፎቶውን ታያላችሁ።

86 ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ በዚያ ቆሞ ነበር፡ ትንሽ አረንጓዴ መኪና፡ በመንገድ ላይ እየሮጠ አየሁ፡ ተንሸራተተም። ወደ ኋላ፡ ዞሮ፡ ዛፍ መታ። አንዲት ወጣት፡ ባለ ወርቃማ-ጸጉር ልጅ... ጀርባዋ ተሰበረ። እኔም፡ “አንድ ትንሽ አረንጓዴ መኪና፡ ወደ ዛፍ ሲንሸራተት አየሁ፡ አሥራ ሰምንት ዓመት ገደማ የሆናት ወጣት ወርቃማ-ጸጉር ልጅ ጀርባዋ ተሰብሯል። በከባድ ሁኔታ ላይ ነች” አልኩ። ማንም ምላሽ አልሰጠም። እኔም በዚያ ሰፊ፡ ትልቅ ታዳሚዎች መካከል በየትኛውም ቦታ እሷን ማየት አልቻልኩም ነበር። በዚያም ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ቆምኩ። እንዲህ አልኳቸው፡ “ተረዱት። ይህን እ... አትጠራጠሩ። ይህ ጌታ ኢየሱስ፡ በትንሣኤው ኃይል ነው። ሥራውን እንዲቀጥል መንፈስ ቅዱስን ላከ።” በዚያም ራእዩ ዳግመኛ ሲሆን አየሁ። ወጣቷን ግን ማየት አልቻልኩም ነበር።

87 ልክ በዚያ ሰዓት፡ በዚያን ጊዜ ከፊት ለፊቴ፡ በፎቶው ላይ እንደምታዩት፡ ብርሃኑ እዚያ ቆመ። እዚህ ቆመ። ወደዚያ ሄድኩና፡ እዚያ ተኝታ ነበር፡ ከመድረክ በታች። እኔም፡ “አንቺ ወጣት ሴት፡ ጌታ ኢየሱስ ፈውሶሻል” አልኳት። እሷም ማልቀስ ጀመረች።

88 እናቷም፡ “ኡህ፡ አይሆንም! ተነሺ እንዳትላት!” እርሷም፡ “ከተንቀሳቀሰች፡ ትሞታለች” አለች።

89 ወጣቷም እየጮኸችና፡ እግዚአብሔርን እያመሰገነች፡ ተነሥታ ቆመች። እናቷም ልጃገረድዋ ተኝታ በነበረችበት አልጋ ላይ ወድቃ ራሷን ሳተች።

ይህ ምንድን ነው?

90 በወቅቱ፡ አንድ ተቺ ሰው ተነሥቶ፡ አንደኛው እግር በአንድ ወንበር ላይ፡ ሌላኛው እግር ደግሞ በሌላ ወንበር ላይ ቆሞ፡ እንዲህ አለ፡ “አንተ፡ አሜሪካዊ! ይህን የምታደርገው በምን ሰም እንደሆነ እንድትነግረኝ እጠይቅሃለሁ! ከየትኛው የሃይማኖት ተቋም አባል ነህ? ” እያችሁ?

91 ተመሳሳይ ነገር ነው። አይረዱም። እነዚህን ነገሮች አይፈልጉም። አብያተ ክርስቲያናት የጌታን መምጣት አይጠብቁም። መንፈስ ቅዱስም የእርሱን መምጣት ለማረጋገጥና፡ እንዲፈጸም ለማድረግ እዚህ መጣ። እጅግ...

ሁሉም የራሱን መንገድ መከተል ይፈልጋል። እዚያ የነበረው ሁኔታም ይኸው ነበር። እያንዳንዱ ቡድን የራሱ የሆነ ሃሳብ ነበረው።

92 የዛሬው ጥያቄ ግን ይህ አይደለም። የምናገረው ስለዚህ ጉዳይ አይደለም። ነገር ግን እኔ የምጠይቃችሁ ጥያቄ፡ ለእናንተ ምን ይመስላችኋል? ይመለከታችኋል። ይህ አገራት ከፍ-እና-ዝቅ የሚያደርግ ማን ነው? ከሰዎች አይደለም። ሰዎች እነዚህን ነገሮች ማድረግ አይችሉም። በጉባኤው ውስጥ ለሚገኘው ህዝብ፡ “**እዚህ** ያለኸው፡ **እዚያ** ያለኸው” እያለ፡ የሚናገረው ይህ ማን ነው፡ በሰብሰባው ላይ የተለያዩ ቦታዎች፡ ሴቶችና ወንዶች እየሞቱ ወደዚህ ሲመጡ፡ እንደዛ የሚለው ማነው? ይህ ማን ነው?

93 ከሦስት ሳምንታት በፊት በካንሰር እየተሰቃየች ሰትሞት የነበረችው፡ ዛሬ ጠዋት ወደ ጥምቀት የገባችው፡ ያቺ ወጣት ሴት፡ እዚህ ሜፕል ጐዳና ላይ የምትኖረው፡ ወይዘሮ ቤቲ ትባላለች። እኔም ከእሷ ጋር የነበሩትን ሦስት ሐኪሞች ጠየቅኳቸው። አንድም የመኖር እድል አልነበራትም፡ ከአራት ወይም ከአምስት ትንንሽ ልጆች ነበሯት፡ እናቴ እነሱን ለመንከባከብ እየሞከረች ነበር። እናቴ፡ “ቢል፡ ከዚህ በኋላ ወደ ቤት አትመለሰም” አለችኝ።

94 እኔም ወደነበረችበት ሄድኩና፡ ጌታ ኢየሱስ ተናገረኝ፡ “**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ ወደ ቤተክርስቲያን ሄዳ በጌታ በኢየሱስ ስም ለመጠመቅ ቃል ከገባችና፡ እግዚአብሔርን ካገለገለች፡ ወደ ቤቷ ደህና ሆና፡ ትሄዳለች።”

እኔም እንዲህ ብዬ ጠየኳት፡ “ይህን ታደርጊያለሽ፡ እመቤት? ”

95 እሷም፡ “የምትለኝን ሁሉ፡ አደርጋለሁ” አለችኝ። ወዲያው ህመሙ ተዋት። ከሦስት ቀናት በኋላ፡ ወደ ቤቷ ተመለሰች፡ ሐኪሞቹም ምንም ዓይነት የካንሰር ምልክት አላገኙም።

96 በጌታ ስም የሚመጣው ይህ ማን ነው? ማን ነው? የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው። ስለዛ ሃሳባችሁ ምንድነው? ፓስተራችሁን ማወቃችሁ፡ ምን ይመስላችኋል? እዚህም በእነዚህ መቀመጫዎች ላይ ሰትቀመጡ፡ ከከተማ ውጭ ያሉ ሰዎች፡ የሚጥል በሽታ ያለባቸው፡ ከ... እዚህ አንድ ሰው ተቀምጧል፡ እዚህ ውስጥ የሆነ ቦታ፡ ሜኖናይት ወንድም፡ እዚሁ፡ በሚጥል በሽታ ህመምተኛ። እሱን አላውቀውም ወይም አይቼው አላውቅም፡ ስለሱ ምንም አላውቅም። በድንገት፡ ከሁለት ዓመት ገደማ በፊት ነው ብዬ፡ እገምታለሁ፡ ወይም እንደዛ ነገር፡ አዎ፡ ከሁለት ዓመት በፊት፡ መንፈስ ቅዱስ ጠራው፡ እንዲህም አለ “**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**።” ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ምንም በላዩ አልነበረም። ይህ ማነው? ይህ ማነው?

97 ይህች ሴት ባለፈው እሁድ፡ እዚህ ተቀምጣ ነበር፡ ለመጨረሻ ጊዜ እዚህ በነበርኩበት ጊዜ፡ ከኢሊኖይ የሆነ ቦታ መጥታ ነበር። በቀጣዩ ቀን... በሰውነቷ ውስጥ ትልቅ እጢ ነበረ፡ ያ አደገኛ ነበር። በኢሊኖይ ከሚገኙት ምርጥ የህክምና ሳይንስ ባለሙያዎች መካከል አንዳንዶቹ፡ ሰኞ ዕለት ቀዶ ጥገና ለማድረግ፡ ወደ አንድ ትልቅ ክሊኒክ እየወሰዷት ነበር። እሷም ወደ ውስጥ ዘልቃ ገባች። በህይወቴ ዘመን ሁሉ፡ አልሰማኋትም ወይም አላየኋትም። በድንገት፡ መንፈስ ቅዱስ ተገለጠላት፡ ማንነቷንና ነገራት፡ ከየት እንደመጣች ነገራት፡ በቀጣዩ ቀን ቀዶ ጥገና ልታደርግ እንደነበረ ነገራት። በወቅቱ ይህን

ለማየት እዚህ የነበሩት፡ ሰንቶቻችሁ ናችሁ? ዜናውን ተመልሰው ሲነገር አያችሁ። በቀጣዩ ቀን፡ ወደ ሐኪሙ በሄደች ጊዜ፡ ከክሊኒክ ወደ ክሊኒክ ወሰዷት፡ ምንም ነገር ማግኘት አልቻሉም።

98 ይህ ማን ነው? ኦህ፡ እግዚአብሔር ይራራልን! ይህን የሚያደርገው ይህ ማን ነው? ይህ ፓስተሬ ነው ለማለት ትደፍራላችሁ? በጭራሽ። በዚህ ጉዳይ ላይ ሰዎች ተሳትፎ አድርገዋል ለማለት ትደፍራላችሁ? በጭራሽ። መንፈስ ቅዱስ ነው፡ በጌታችን በኢየሱስ ላይ የነበረውን መንፈስ። ከቤተክርስቲያኑ ጋር ራሱን አንድ ለማድረግ መምጣቱ፡ ታላቅ ቅዱስ ብርሃኑን ለመዘርጋት፡ ለመበዝበት፡ የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን፡ ወደ ኅብረት ለማምጣት በጣም ተቃርቧል፡ ንጥቀት ተቃርበዋልና። አሜን!

99 ይህ ማን ነው? መልስ ልሰጣችሁ አልችልም። መልስ ልሰጣችሁ አልችልም። ነገር ግን ለራሴ መልስ መስጠት እችላለሁ። ዛሬ ማታ፡ በዚህ የተቀደሰ መሰዊያ ላይ፡ በዚህ ሕዝብ ጆሮ፡ ሁሉንም፡ በጌታችን በ—በኢየሱስ ደም በተገዙ ሰዎች ፊት፡ ይህን የምናገረው ከልቤ ጥልቀት ነው። ከእናንተ አንዱ ስለሆንኩ አይደለም፡ የተለየ ሰው ስለሆንኩ አይደለም፡ ነገር ግን በደም ከታጠቡት የተዋጁት ውስጥ አንዱ ነኝ። ዛሬ ማታ፡ በዚህች ቤተክርስቲያን ውስጥ፡ ከላይ የሚያበራው ተመሳሳይ ብርሃን፡ ያው የሚያሳየው፡ በተፈጥሮው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ መልክ መሆኑን ነው ብዬ አምናለሁ።

100 መጽሐፍ ቅዱስን የሚያውቅ ማንኛውም ሰው፡ ኢየሱስ፡ "ከእግዚአብሔር መጥቻለሁ ወደ እግዚአብሔርም እሄዳለሁ፡" ብሎ እንደተናገረ ያውቃል። በሥጋ ከመገለጡ በፊት፡ ከሙሴ ጋር በምድረ በዳ በነበረበት ጊዜ፡ የእሳት ዓምድ ነበር። ሙሴም እርሱን ማየት በፈለገ ጊዜ፡ የጀርባዎቹን ክፍሎች አሳየው። ሙሴም፡ "የሰው ይመስላል" አለ። እዚህ ምድር ላይ በነበረ ጊዜ፡ ሰው ነበር። በዛሬው ጊዜም፡ በተበዣቸው ሰዎች አማካኝነት፡ ተመሳሳይ ነገር አድርጓል። እዚህ መጥቶም እነሆ ፎቶግራፍ ተነስቷል። ይህ ምንድነው?

101 ከሞቱ፡ ከቀብሩና ከትንሳኤው በኋላ፡ አንድ ቀን፡ ጳውሎስ ወደ ደማስቆ እየተጓዘ ሳለ፡ ታላቅ ብርሃን መታው። በዙሪያው የነበሩት ሰዎች ብርሃኑን አላዩትም ነበር። ይሁን እንጂ ጳውሎስ ዓይነ ሰውር እስኪሆን ድረስ፡ ብርሃኑ መታው። በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ከዓይኖቹ ጋር ችግር ነበረበት። አንድ ጊዜ እንዲህ ብሏል፡ "ከመገለጥ ብዛት እንዳልታበይ፡ ይህ ነገር ተሰጠኝ፡" በሥጋው ውስጥ እንደ እሾህ ሆኖ፡ እንዲመታው፡ የሰይጣን መልእክተኛ ሆኖ ተላከለት። ምክንያቱም የተገለጠው ነገር የተትረፈረፈ ነበር።

102 ጳውሎስም በተመታ ጊዜ፡ እጅግ ድምጻቸውን ያበዙትን ሕዝብ ሊያሳድድ በመንገዱ ላይ ነበር፣ ዳግመኛ-የተወለደ ቡድን፡ መናፍቃን የተባሉ ሰዎችን ሊያሳድድ በመንገዱ ላይ ነበር። ጳውሎስ እነዚህን ሰዎች በኪሱ ወረቀት ይዞ ለመያዝና፡ ወደ ኢየሩሳሌም ለማምጣት፡ በመንገድ ላይ ነበር። እኩለ ቀን አካባቢ፡ አንድ ብርሃን ወደ ምድር ወረደ፡ እግሩን ወደ መሬት፡ መታው፡ በምድርም ትቢያ ውስጥ ወደቀ። ከዚያ ብርሃን እንዲህ የሚል ድምፅ መጣ፡ እንዲህ አለ፡ "ሳውል፡ ሳውል፡ ስለ ምን ታሳድደኛለህ?"

103 በዚህ ጊዜ ሳውል ዞረ፡ ዓይነ ስውር ሆኖ፡ ወደ ላይ ተመለከተ። ታላቁንና፡ የከበረውን ብርሃን ማየት ችሎ ነበር። እሱም "ጌታ ሆይ፡ አንተ ማን ነህ?"

አለው፡

104 ኢየሱስም እንዲህ አለ፡ “እኔ ኢየሱስ ነኝ። ከእግዚአብሔር መጥቼ፡ ወደ እግዚአብሔርም ሄድኩ። ከእግዚአብሔር መጥቻለሁ፣ ወደ እግዚአብሔር እመለሳለሁ።” “የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብሰብሃል፡” አለው።

105 በዚያ በተቀደሰ አሸዋ ሰፍራ ላይ አንድ መገለጥ ሲያገኘው፡ ሰው አንድ ጊዜ በዚያ ቦታ ከተነካ፡ በፍፁም ተመሳሳይ ሊሆን አይችልም። አንድ ሰው፡ ራሱን ክርስቲያን ብሎ ከመጥራቱ በፊት ራሱን መለየት ከመቻሉ በፊት፡ በመጀመሪያ ከ-በረሃው-ጀርባ-ልምምድ ሊኖረው ይገባል፡ እግዚአብሔርንም ፊት ለፊት፡ የተገናኘበት ቦታ።

106 ለዛሬ፡ ማንኛውም ዓይነት መልስ፡ ሊኖራችሁ ይችላል። ጌታ ያዘዘውን በትክክል ሲፈጽም ማየት ትችላላችሁ፡ ብልህ የሆኑ የሃይማኖት ምሁራን ያብራራሉ። እንዲህ ይላሉ፡ “ያ ለሌላ ዘመን ነበር። **ለዚህ** ነበር። ወይም፡ ለሌላ ዘመን ነው። ወይም፡ የተሳሳተ ነው።” ስለ ኢየሱስ እንደተናገሩት፡ “እርሱ ቡኤልዜቡል ነው፡ ዲያብሎስ ነው። ፣ እሱ ጠንቋይ ነው” እዳሉት ነው። ለእነዚህ ሁሉ ነገሮች መልስ አላቸው።

107 ነገር ግን አንድ ሰው ከክርስቶስ ጋር ሲገናኝ፡ እንደ ጳውሎስ እርሱን ሲያየው፡ ወይም ሲያጋጥመው፡ ያንን ተሞክሮ ለሰው ለማስረዳት የሚያስችል በቂ የሃይማኖት ምሁራን በዓለም ላይ አይኖሩም።

108 ለዚህም ነው፡ ዛሬ፡ ተሞክሮ የሌላቸው። ለዚህም ነው መናገር የማይችሉት… ሁሉም “ይህ ማን ነው? ይህ ምንድን ነው? ከየት ነው የመጣው? ” እያሉ ነው፡ መልስ የላቸውም። ለምን? ምክንያቱም የሚያውቁት የሆነች ቤተክርስቲያን ያዘጋጀችውን ሥነ መለኮት ትምህርት ብቻ ነው። “ቲኦሎጂን ማወቅ” ሕይወት አይደለም። “መጽሐፍ ቅዱስን ማወቅ” ሕይወት አይደለም።

109 “እሱን ማወቅ” ሕይወት ነው። እንደ ግል አዳኝህ “እሱን ማወቅ”፡ በመገኘቱ እንደሞላህ ማወቅ ሕይወት ነው። በሆነበት ጊዜ እዚያ ነበራችሁ። ማንም ሊወስድባችሁ አይችልም። ማንም እያብራራላችሁም። ይህ ተሞክሮ በሚያጋጥማችሁ ጊዜ፡ እርሱ ማን እንደሆነ ታውቃላችሁ። ለእኔ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፡ ዛሬና፡ ለዘላለም ያው ነው።

110 ይህን ተአምር የሚያደርገው ይህ ማን ነው? እነዚህን ታላላቅ ሥራዎች የሚያከናውነው ይህ ማን ነው? ሰባኪው ነው? ኦራል ሮበርትስ ነው? ቢሊ ግራሃም ነው? ጃክ ሹለር ነው? ዊልያም ብራንሃም ነው? ማንም ይሁን ማን፣ ምንም የሚያደርጉት ነገር የለም። እነርሱ መሣሪያዎች ናቸው።

111 ሕዝብን ለማዘጋጀት በምልክቶች፡ በድንቆችና በተአምራት፡ መንፈስ ቅዱስ ከወንጌል ጋር እየመጣ ነው። አየሩ በተሰፋ የተሞላ ነው፡ አማኞች መምጣቱን ይጠብቃሉ።

112 ሌሎች ደግሞ፡ “እነዚህ ሪቫይቫል ለምን? ሪቫይቫል ለምን እናደርጋለን? ቤተክርስቲያንን እናቋቁም” ይላሉ። ለምን፡ እዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ እንደተነገረው፡ ይህም፡ አዲሱን ቤተክርስቲያን መገንባት ሰንጀምር፡ እንዲህ

ተብሏል፡ “ተአምራትን አንፈልግም። ከእንግዲህ እነዚህን ነገሮች አንፈልግም። እነሱን ከፈለጋችሁ፡ ወደ የሚሆንበት ቦታ ሂዱ። እዚህ አያስፈልጉንም።” የብራንሃም ተብርናክል ወደዚያ ዝቅተኛ ቦታ ስትወርድ፡ ትሰምጣለች።

113 ይህች ቤተክርስቲያን የተመሰረተችው በኢየሱስ ክርስቶስ መርሆዎች ኃይልና በወንጌል ላይ ነው። ይህ ተብርናክል እስካለ ድረስ፡ ክብር ያለው መንፈስ ቅዱስ፡ ለማዳን፡ በመንፈስ ቅዱስ ለሞሙላት፡ የታመሙትን ለመፈወስ ወደ ነፍሳት ይድረስ። ለእኔ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናም፡ ዛሬና፡ ለዘላለም ያው ነው።

እንጸልይ።

114 እርሱ ማን እንደሆነ ካላወቃችሁ፡ ይህ ሁሉ ምን ማለት እንደሆነ ካላወቃችሁ፡ ማወቅ ከፈለጋችሁ፡ እጃችሁን ታነሳላችሁ? እጃችሁን በማንሳት፡ እንዲህ በሉ፡ “ወንድም ብራንሀም፡ እርሱን እንዳውቅ፡ ጸልይልኝ።” ጌታ ይባርካችሁ። በዙሪያው ሁሉ፡ እጆችን አያለሁ።

115 አሁን፡ የሰማይ አባት ሆይ፡ ይህንን መልእክት፡ እና የሰዎችን እጆቻቸውን ወደ ላይ ያነሱትን ፍሬዎች እናመጣለን፡ ይህም ማን እንደሆነ ለማወቅ ፈልገው ነው። ከታላቁ ኢየሱስ ጋር መተዋወቅ ይፈልጋሉ። ይህም፡ መምጣቱ፡ ሕመምተኞችም መፈወስ እስኪጀምሩ ድረስ፡ ትንሣኤ፡ እጅግ ቀርቧል። ይህ ከተፈጸመ በኋላም፡ ትንቢት ወደ ቤተ ክርስቲያን መጣ፡ ከዚያም ሰጦታዎችና ተአምራት፡ አሁን ደግሞ እስከ መጨረሻው ምልክት ድረስ። ቀጣዩ ይመጣል፡ ይህም መነጠቅ ነው፡ ቤተክርስቲያን ትወሰዳለች። እኛም፡ ጌታ ሆይ፡ በትንሳኤህ ኃይል አንተን አውቀናል የምንል፡ እንጠብቃለን፡ እንፈልጋለን፡ እንጮኻለን፡ እንለምናለን፡ “ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ና!”

116 ጌታ ሆይ፡ ቤተክርስቲያንህን ንጠቃት፡ ቶሎ ውሰዳት። ምክንያቱም፡ በቅርቡ፡ የሰው ልጆች አንተን ባለመታዘዛቸው፡ እንዲኖሩባት የፈጠረሃቸውን ምድር በቅርቡ ያፈነዷታል። ሰላምን ሳይሆን፡ ጦርነትን ነው የተማሩት። ጽድቅን ሳይሆን፡ ክፋትን ነው የተማሩት። ሁሉም የሥልጣን ጥማት እንዳይሰማቸው እንዴት ማድረግ ይቻላል! ጌታ ሆይ፡ በልባቸው ውስጥ ያ ትንሽ ለሥልጣን እንዲራቡ ያደረጋቸው ቦታ፡ በሆነ ላቦራቶሪ ውስጥ ለማርካት እየሞከሩ ነው፡ ባልንጀራቸውን ለማፍረስ።

117 እግዚአብሔር ሆይ፡ የሚናፍቁት ኃይል የእግዚአብሔር ልጅ የትንሳኤ ኃይል የመንፈስ ቅዱስ ኃይል፡ ሕይወታቸውን ለመለወጥ መሆኑን ቢገነዘቡ ኖሮ፣ ህዝብን አያጠፉም፡ ነገር ግን ሕይወታቸውን ለመለወጥ አገልጋዮችህም እንዲሆኑ አድርጋቸው።

118 ብዙ ሰዎች፡ በመጥፎ ሃሳቦች ተይዘዋል፡ እኛን “ምንም የማያውቁ፡” እ—እና ልክ በመጀመሪያዎቹ ዘመናት እንዳደርጉ “መናፍቃን፡” እንደሆንን አድርገው ይገልጹናል። እነርሱ ግን ደስ እያላቸው፡ እያመሰገኑ፡ ሲመለሱ ስለ ስምህን ነቀፋ መሸከም ችለዋል። ዛሬ ማታ፡ ጌታ ሆይ፡ በሁሉም ቦታ፡ የሚገኙት ልጆችህ የሚሰማቸው ስሜት ይህ ነው። ደስተኞች ብቻ ነን።

119 በዘመንህ የነበሩ አንዳንድ ሰዎች አንተን ለመለየት ሞክረዋል። እንዲህ አሉ፡ “የዚያ የጫካው ሰው የዮሐንስ ወዳጅ ነው፡ ዮሐንስ፡ ልብስ ሳይለብስ ከጫካ የመጣው፡ የድሮ የበግ ቆዳ ብቻ ጠቅልሎ ነው የመጣው። ቃሎቹን

እየተናገረ አንድ የጫካ ሰው፡ ከምስራቅ እና ከምዕራብ፡ ‘ምሳር በዛፉ ሥር ተቀምጧል፡” ይላል።’ “እሱም የ—የእሱ ተከታይ ነው። እሱ የጫካ ሰው ነው። እሱ እብድ ነው። አእምሮውን አጥቷል፡” አሉ። ጌታ ሆይ፡ ከአንተ ጋር የነበረው ከተፈጥሮ በላይ የሆነ አገልግሎት፡ የእነዚያን ሰዎች ዓይን አሳውሯል።

120 ይህ ታላቅ መንፈስ ቅዱስ በዘመኑ፡ እንደ ዮሐንስ የጌታን መምጣት አስቀድሞ በማወጅ፡ ማየት ለማይፈልጉት ሰዎች ዓይነ ሰውር አድርጎአል፡ ህዝቡን እያሳወረ፡ ማየት ለማይፈልጉት። ለመመልከት ፈቃደኞች ለሆኑት ግን፡ አንተ መርጠሃቸዋል። “አባቴ የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፡” ብለህ ነግረኸኛ ነበር፡ “ከእነርሱም አንድ ስንኳ አይጠፋም። እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።” ለዚህም እናመሰግናለን።

121 ዛሬ እጃቸውን ላነሱ፡ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ በትንሣኤው ኃይል፡ እራስህን፡ እንድታሳያቸው እንጸልያለን፡ በልምምድ፡ በትንሣኤ ኃይል አሳያቸው። አድርገው፡ ጌታ ሆይ።

122 እዚህ ላይ እጃቸውን ያልዘረጉ ሌሎችም ሊኖሩ ይችላሉ፡ ነገር ግን፡ በልባቸው ውስጥ፡ እንደሚያስፈልጋቸው ያውቃሉ። ልባቸው የሚፈልገውን ሁሉ፡ እንድትሰጣቸው እጸልያለሁ።

123 ዛሬ ማታ ከህንጻው ስንወጣ፡ የተለዩ ሰዎች ሆነን እንሂድ። ወደዚህ የመጣንበት ዓላማ፡ ከእግዚአብሄር ፈቃድ ጋር የሚቃረን ከሆነ፡ ከነበረን በተለየ አላማ ይዘን መሄድ ይሁንልን። ከአንተ ጋር ተሞክሮ ማግኘታችንንና ስለ ማን እንደምንናገር ስለምናውቅ፡ ከእርሱ ጋር ስለተገናኘንና ስላወቅነው ከእርሱ ጋር ኅብረት ስላለን፡ ነፍሳችን እስክትረካ ድረስ፡ በመሠዊያው ቀንዶች ለመያዝ፡ በቁርጠኝነት እንሂድ። አባት ሆይ፡ እነዚህን ነገሮች ሰጠን። የታመሙትንና የተሰቃዩትን ፈውስ።

124 ውድና ተወዳጅ ፓስተራችንን ባርክልን። ጌታ ሆይ፡ ወንጌልን ሲዘምሩና፡ በሬዲዮ ሲሰብኩ፡ አንተ ከእርሱና ከእህቶቹ ጋር እንድትሆን እንጸልያለን።

125 በሮቻችን ውስጥ ያሉትን እንግዶች ባርካቸው። ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ በልባቸው ላይ፡ ሸክም ይዘው ይሂዱ፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ፡ አንተን የማያውቁና፡ ከዚህ በፊት፡ የማያገለግሉ ቢሆኑም እንኳ፡ አንተን እንዲያገለግሉህ ዓላማችን ነው። ይህን እናውቃለን፡ ይህም፡ “ሌሎቹ ነገሮች ሁሉ ከንቱ ይሆናሉ፡ “የጌታ ቃል ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።” ይሁን፡ አባት ሆይ።

126 ኃጢአታችንን ሁሉ፡ ይቅር በለን። በታላቁ… መገናኘት ይሁንልን [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]

ቀድሞ ስለወደደኝ
መዳኔንም ስለገዛ
በቀራንዮ መስቀል ላይ።

127 አሁን፡ ከመልዕክቱ በኋላ፡ ራሳችንን ዝቅ አድርገን እናምልከው፡ እየዘመርንለት።

እወደዋለሁ፡
በሙሉ ልብህ።
እወደዋለሁ

ቀድሞ ስለወደደኝ
መዳኔንም ስለገዛ
በቀራንዮ መስቀል ላይ።

128 ስንቶቻችሁ ናችሁ በእውነት የምትወዱት? እጃችሁን አንሡ፡ ይህን በምስክርነት ተናገሩ፡ "እወደዋለሁ" በሉት። ኦህ፡ ድንቅ አይደለምን? ታውቃላችሁ፡ በሆነ መንገድ፡ ልክ እንደዚህ ሆኜ፡ መገኘቱን መጠጣት እወዳለሁ። ቃሉ፡ ሲወጣ፡ ወደ ልባችን ይወርዳል። ያስተካክለናል። ለመንፈሱ እንድንገዛ ያደርገናል። ታዲያ እርሱን ማምለክ እንዴት ያለ ደስ የሚል ነገር ነው! አሁን፡ ዛሬ ማታ፡ ከቤተ ክርስቲያን፡ ስትወጡ፡ ሄዳችሁ አምልኩት።

129 በዚህ ሳምንት፡ ረቡዕ ምሽት የጸሎት ሰብሰባ እንደሚደረግ፡ አስታውሱ። ወንድም ኔቪል እሁድ፡ ወይም ቅዳሜ፡ ዘጠኝ ሰዓት ላይ በWLRP ላይ፡ የሚያስተላልፈውን ፕሮግራም አትርሱ። እነሱን መስማት እወዳለሁ፡ አትወዱም? ኳርቴት፡ ወይም ትሪዮው፡ በጣም መልካም ይመስላሉ። እኔና ባለቤቴ፡ እንዲሁም ልጆቼ፡ ትንሽ ሬዲዮው ገዝተን በ—በዙሪያው ቁጭ ብለን፡ ወንድም ኔቪልንና፡ ስርጭቱን፡ የሚወደውንና የሚያምንበትን አምላክ፡ እንዴት ከፍ እንደሚያደርገው እሰደናቂ ቃሉን እናዳምጣለን። ይህን...

130 እናንተ እንግዶች፡ ቤተክርስቲያን ከሌላችሁ፡ ኑና ተቀላቀሉን። እላችኋለሁ፡ ይህን የሚናገረው እርሱ እዚህ ስለተቀመጠ ነውን። አይደለም፡ ወዳጄ። ይህን፡ ብዙ ጊዜ ተናግሪያለሁ። ወንድም ኔቪልን እወዳለሁ። ይህ፡ በመጀመሪያ፡ እሱ የሃይማኖት ምሑር ነው። በመጀመሪያ፡ እሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። የሚቀጥለው ነገር፡ ሁሌም ያው ነው። ለዓመታት አውቀዋለሁ። ፈጽሞ አልተለወጠም፡ ትንሽ እንኳን። አሁንም ኦርማን ኔቪል ነው፡ የጌታ ኢየሱስ አገልጋይ ነው። እንደማስበው...

131 ባለፈው ምሽት፡ በፕሮግራሙ ውስጥ፡ መጥተን ለታመሙ መጸለይ፡ የምንችልበት ቦታ መሰጠት ይችል እንደሆነ፡ ለመጠየቅ ደወልኩለት። ታውቃላችሁ፡ በዚህ ጠዋት፡ ሰዎች ሲገቡ ነበር። ምስኪን ሚስቱ ስልኩን መለሰች፡ ስለ ጉዳዩ ከባለቤቴ ጋር፡ እዚያ፡ እየተነጋገርኩ ነበር።

132 እንዲሁም አምላክን ስለ ቆንጆዋ ሚስቱና ስለ ቤተሰቡ ምን ያህል እንደምናመሰግነው። ያ በጣም ጥሩ ነው። አንድ ፓስተር እና ሚስቱ እንደዚያ ሲግባቡ ስታዩ፡ በጣፋጭነትና በትሕትና፡ ያ ቤተክርስቲያኗን በጣም የተሻለች ያደርጋታል። ቀኖቹ እያለፉ ሲሄዱ ይበልጥ ጣፋጭ እየሆነ ይሄዳል።

133 በሙሉ ልባችሁ ትወዱታላችሁ? መልካም። **የኢየሱስን ስም ይዘህ ሂድ** የሚለውን፡ የመጨረሻ መዝሙር እንዘምራለን። እህታችን፡ በመፅሃፉ ውስጥ ካገኘሽው፡ ፒያኖ ተጫወችልን። አሁን የመጨረሻ መዝሙራችንን እንዘምራለን። የመጀመሪያውን ስንኝ ስንዘምር፡ ዞር ብለን፡ እጃችንን እንድንጨባበጥ እፈልጋለሁ። ደህና። ኮርዱን ስጠን።

... የኢየሱስ ስም ካንተ ጋር ይዘህ ሂድ፡
የሀዘንና የዋይታ ልጅ፣
ደስታ እና ምቾት ይሰጣል፡
በሄዳችሁበት ቦታ ሁሉ ውሰዱት።

ውድ ስም፡ እንዴት ጣፋጭ ነው!

የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፣ (እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ።)
ውድ ስም፡ እንዴት ጣፋጭ ነው!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

ይህን ስንኝ አሁን እንዘምር፡

በኢየሱስ ስም እንሰግዳለን፡
በእግሩ ተደፍተን እንሰግዳለን፡
በሰማይ የነገሥታት ንጉሥ አድርገን እንሾመዋለን፡
ጉዟችን ሲጠናቀቅ። (ያ ድንቅ አይሆንም? )

ውድ... (የከበረ ስም!) ኦህ እንዴት ጣፋጭ ነው!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፣
የከበረ ስም፡ (የተከበረ ስም!) ኦህ እንዴት ጣፋጭ ነው!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ...

134 **የቤተሰብን ጸሎት እትርሱ** የሚለውን መዝሙር፡ ሰንቶቻችን እናስታውሳለን? ታስታውሳላችሁ? ቴ... ቴልማ፡ ይህን ታውቂዋለሽ፡ ወይም ኮርዱን፡ ወይም አታውቂውም? እስቲ አንዴ እንሞክር። አታስታውሱትም? ምናልባት... እኔ ከእናንተ ጋር አንድ ጊዜ መሞከር እችላለሁ።

የቤተሰብ ጸሎት አትርሱ፡
ኢየሱስ እዚያ ሊገናኛችሁ ይፈልጋል፣
ሸክማችሁን ሁሉ ይወስደዋል፡
ኦህ፡ የቤተሰብ ጸሎት አትርሱ።

135 ሰንቶቻችሁ የበተሰብ ጸሎት አላችሁ? ይህ ጥሩ ነው። እስቲ እንደገና እንሞክር። ወደዚህ እመልሰዋለሁ። ወድጄዋለሁ። ሁላችንም አንድ ላይ፡

የ—የቤተሰብ ጸሎትን አትርሱ፡
ኢየሱስ እዚያ ሊገናኛችሁ ይፈልጋል፣
ሸክማችሁን ይወስደዋል እሱ፡
ኦህ፡ የቤተሰብ ጸሎት አትርሱ።

136 ኦ ጌታ ሆይ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተፅፏል፡ ከጳውሎስ የእጅ መሃረቦችንና ወይም መጎናጸፊያዎችን ወሰደው፡ እርኩሳን መናፍስት ከሕዝቡ ሄዱ፡ በሽታዎችም ተፈወሱ። ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ ለችግረኞችና ለታመሙ ሰዎች እልክላቸዋለሁና፡ በእነዚህ ሰዎች ላይም፡ ተመሳሳይ ነገር እንዲፈጸም፡ እንጸልያለን። በሀገሪቱ ውስጥ፡ የሆነ ቦታ ይህ እንዲሆን የሚጠብቁና የሚፈልጉ ሰዎች አሉና። አባት ሆይ፡ በልጅህ፡ በኢየሱስ ስም እንድትሰጠን፡ እጸልያለሁ። አሜን።

137 አሁን የምጠይቃችሁ፡ ራሳችንን እንዳጎነበሰን፡ ከቸርች ኦቭ ጋድ፡ በጣም ውድ የሆነው ወንድማችን ሰሚዝ፡ ልክ እንደ ወንድማችን ኔቪል፡ ግልጽ፡ ታማኝ፡ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆኖ፡ ያገኘነው፡ በመጪው ሳምንት እንዲቀጥል፡ በረከቱን እንዲለምንላችሁ እጠይቃለሁ። ዳግመኛ እስክንገናኝ፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ወንድም ሰሚዝ።

[ወንድም ሰሚዝ ጸለየ—አርታዒ።] አዎ፡ ጌታ ሆይ። አድርገው፡ ጌታ ሆይ። አዎ። አዎ። አዎ። አዎ። ኣሜን።

138 እርስ በርሳችሁ እጃችሁን ተጨባበጡ። በድጋሜ ወደ ተብርናክል፡ እንኳን ደኅና መጣችሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

59-0510E ይህ ማን ነው?
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org